# ጋዜጣዊ መግለጫ

## በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን ለመታደግ አስቸኳይ የሲቪል ማህበራት የጋራ ጥሪ!

## መስከረም 07/2013

እንደሚታወቀው በርካታ የሀገራችን ዜጎች እንጀራን ፍለጋ እና የቤተሰቦቻቸውን ኑሮ ለማሻሻል ሲሉ ወደ ተለያዩ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች በህጋዊ እና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ይሄዳሉ። ከእነዚህ ዜጎች አንዳንዶቹ በለስ ቀንቷቸው ኑሯቸውን በማሻሻል ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው እና ለሀገራቸው ተጨማሪ ገቢ እያስገኙ ቢሆንም ሌሎች ግን በአሰሪዎቻቸው እና በህገ ወጥ ደላሎች ለከፍተኛ ችግር ይጋለጣሉ። ኢትዮጵያዊያን በተለያየ ጊዜ በሚኖሩባቸው ሀገሮች በተለይም በመካከለኛው ምስራቅ ብዙ ችግር ሲደርስባቸው መስማት እንግዳ ነገር አይደለም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የኮቪድ-19 እና ሌሎችም ሰው ሰራሽ ችግሮች የእነዚህ ወገኖቻችንን በበለጠ ለሰብዓዊ መብት ጥሰት እየተጋለጡ ይገኛሉ።

ከዚህም የተነሳ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ከስደት ተመላሾች ከተለያዩ አረብ ሀገሮች በተለይም ከሊባኖስ ወደ ሀገራቸው በመግባት ላይ ይገኛሉ። በቀጣይ ሳምንታትም ይሄው እንደሚቀጥል ይጠበቃል። እነዚህ ተመላሾች ወደሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ በቀጣይ የሚቋቋሙበት ሁኔታ ብዙ ስራ የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም አሁንም በውጪ ሀገር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ኢትዮጵውያን በተለይም ለቤት ውስጥ ስራ የሚሄዱ ሴቶች እጣ ፈንታ ይበልጥ ያሳስባል።

ኑሮን ለማሸነፍና የቤተሰቦቻቸውን ህይወት ለመቀየር ከሀገራቸው የወጡ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን ደመወዝ መክፈል አንችልም ባሉ ቀጣሪዎቻቸው መንገድ ላይ የተጣሉ ኢትዮጵያዊያን መዋያ ማደሪያቸው የቤይሩት ጎዳናዎች ላይ ሆነዋል። ሴት ኢትዮጵያዊያን ለቅጥር በብዛት ከሚሄዱባቸው ሀገሮች ሊባኖስ አንዷ ስትሆን የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ቀውስ እና ወቅታዊው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ተደማምረው የእነዚህን ዜጎቻችንን ህይወት የተወሳሰበ ችግር ውስጥ ጥለውታል። ጥቂት የማይባሉ ዜጎች አማራጭ በማጣት ያለክፍያ እያገለገሉ በአሳዳሪዎቻቸው ቤት መቆየትን መርጠዋል። በአሰሪዎቻቸው የተለያየ ጥቃት ተፈጽሞባቸው መንገድ ላይ የተተዉ እና ወደ ሀገራቸው ለመመለስ በቂ ገንዘብ፣ ፓስፖርት እና ሌሎች አስፈላጊ የጉዞ ሰነዶችን የሌላቸውም ይገኙበታል።

ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ የተፈጠረው የአለም ዓቀፍ በረራዎች ውስንነት በተመሳሳይ ችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎቻችን ባለፉትን በርካታ ወራት ለተጨማሪ ኢሰብዓዊ ጥቃቶች እየዳረጋቸው ሲሆን ከሚደርስባቸው ጥቃት እና እንግልት የተነሳ የከፋ ስነ ልቦናዊ ቀውስ ውስጥ የሚገኙ እና ራሳቸውን የሚያጠፉ ኢትዮጵያዊያን መኖራቸው ከየአካባቢዎቹ የሚወጡ ሪፖርቶች ያመለክታሉ።

ከአሳዛኙ የቤይሩት ፍንዳታ ክስተት አስቀድሞም በኢኮኖሚያዊ ቀውስ ውስጥ የነበረችው ሊባኖስ አሁን የምትገኝበት ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ በዚያ ለሚገኙ የውጪ ሀገር ሰራተኞች ተስፋ የሚሰጥ አይደለም። በሀገሪቱ እየተባባሱ የመጡት የኑሮ ውድነት፣ ድህነት እና ስራ አጥነት በቀጣይም ቀጣሪዎች በስደት የመጡ ሠራተኞቻቸውን እንዲቀንሱ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ግምት አለ። የሊባኖስ ገንዘብ ከዶላር አንጻር የምንዛሬ ዋጋው እየወረደ መምጣትም ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ለሚፈልጉት እና ፓስፖርት ለያዙ ዜጎቻችን ሳይቀር የትራንስፖርት ክፍያው ከአቅማቸው በላይ እንዲሆን አድርጓል።

የሊባኖስ የሠራተኞች ጉዳይ አዋጅ በስደት ወደ ሀገሪቱ በገቡ የውጪ ዜጎች ላይ ተግባራዊ አይደረግም። በሌሎችም የመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች የሚተገበረው የካፋላ ስፖንሰርሺፕ ስርዓት ለበርካታ አመታት ለስደተኛ ሰራተኞች የእንግልት ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። ከዚህ ስርዓት የተነሳ ቀጣሪዎች የሰራተኞችን ፓስፖርት ከመያዝ አንስቶ እንቅስቃሴን እስከመገደብ ብሎም በፈለጉ ጊዜ ወደ ሀገራቸው እንዳይመለሱ እስከመከልከል ይደርሳሉ።

በእርግጥ ይህ አይነቱ ችግር በመካከለኛው ምስራቅ በሌሎችም ሀገሮች ዜጎች ላይ የሚደርስ ቢሆንም በዚያ የሚገኙት ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች በቁጥር ከፍ ያለ እና የተለየ ትኩረት የሚሻ ነው። የሠራተኞችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ ከመካከለኛው ምስራቅና እና ሌሎች ሀገሮች ከ19000 በላይ ኢትዮጵያዊያን ወደ ሀገራቸው መመለሳቸውን የገለጸ ሲሆን በተለይ ከሊባኖስ ከተመለሱት ብዙዎቹ የትራንስፖርት ወጪያቸውን በራሳቸው የሸፈኑ መሆናቸው ይታወቃል።

ወደ ሀገር የመመለስ ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ጨምሯል። ከሶስት ወራት በፊት ሳዑዲ አረቢያ በሀገሯ የሚገኙ እና የጉዞ ሰነድ አልያዙም ያለቻቸውን 12000 ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው እንደምትመልስ መግለጧ የሚታወስ ሲሆን ይህም እስካሁን ወደ ሀገራቸው መመለስ ከቻሉት የሚበልጡ ዜጎቻችንን ለመቀበል መዘጋጀት እንደሚስፈልገን የሚቁም ነው።

እኛ (ስማችን ከታች የተዘረዘረው) የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችና ማህበራት በመካከለኛው ምስራቅ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ጋር በተያያዘ ከአካባቢው ሀገሮች የሚወጡት ሪፖርቶች ይዘት በእጅጉ እያሳሰበን ይገኛል። በቅርቡ የእንግሊዙ ቴሌግራፍ ድር-ገጽ በሳዑዲ አረቢያ በኮቪድ-19 ለይቶ ማቆያ ማዕከሎች የተተዉ አፍሪካዊያን በአብላጫው ኢትዮጵያዊያን ላይ ያወጣውን የምርመራ ሪፖርት መጥቀስ ይቻላል።

በዚህ ወቅት በሺህዎች የሚቆጠሩ ከስደት ተመላሾችን በድንገት መቀበል እና ማስተናገድ ኢትዮጵያ የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝን ለመከላከል በምታደርገው ጥረት ላይ የራሱ የሆነ ጫና ማሳደሩ እርግጥ ነው። ይህም ሆኖ መንግስት ባለፉት ወራት ከሳዑዲ አረቢያ፣ ሊባኖስ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ እና ሊባኖስን ከመሳሰሉ ሀገሮች ችግር ላይ የወደቁ በሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያደረገውን ጥረት እናደንቃለን። ለችግሩ ምላሽ ለመስጠትም ከተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የሲቪል ማህበራት ጋር በትብብር ለመስራት ሙከራዎች እየተደረጉ መሆኑንም እንገነዘባለን።

ይሁን እንጂ በተለያዩ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች ለስራ የተጓዙ ኢትዮጵያዊያን የሚገኙበትን ወቅታዊ ሁኔታ በጣም አሰቃቂ መሆኑን ከግምት በማስገባት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ ጥሪ እናቀርባለን።

**በመንግስት በኩል በአፋጣኝ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፡-**

- ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የሚፈልጉ እና አስፈላጊ ሰነዶችን ማሟላት ያላቻሉ ዜጎችን ለይቶ ጊዜያዊ የጉዞ ሰነድ የሚገኙበትን ሁኔታ እንዲያመቻች እንዲሁም ወደ ሀገር የመመለሱን ስራ ለማቀላጠፍ ርብርብ እንዲያደርግ

- የዜጎች ሰብዓዊ መብት መብት ጉዳይ በሊባኖስ እና በሌሎችም የሩቅ ምስራቅ ሀገሮች በሚገኙ ቆንስላዎች በኩል አስፈላጊው ትኩረት እንዲያገኝ። በሩቅ ምስራቅ ሀገሮች በዜጎች ላይ በሚፈጸሙ እና ሪፖርት በሚደረጉ ጥቃት፣ ግድያ እና ራስ የማጥፋት ሪፖርቶች ላይ ከሀገሮቹ መንግስታት ጋር በመቀናጀት ተገቢ ምርመራ እንዲያካሂድ
- የካፋላ ስርዓት፣ የሠራተኞች መብት፣ ዝቅተኛ ደመወዝ፣ የስራ እረፍት እና የስራ ሰዓት መጠን ጋር በተያያዘ ከመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች ጋር በሚደረግ የሁለትዮሽ ግንኙነቶች መፍትሄ እንዲፈልግ። ለምሳሌ በቅርቡ ካታር የሰራተኞችን የስፖንሰርሺፕ ስርዓት ለመቀየር መወሰኗ መነገሩ እና ሊባኖስን ተመሳሳይ ዝግጅት መጀመሯን እንደአበረታች እንቅስቃሴ ሊወሰድ ይችላል።
- የውጭ ሀገር ስራ እና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በህጋዊ መንገድ ብቻ ስለመስራታቸው ተገቢው ቁጥጥር እና ክትትል እንዲቀጥል።
- ችግር ላይ የወደቁ ዜጎች ወደ ሀገር ከመመለሳቸው በፊት የሚቆዩባቸው ጊዜያዊ መጠለያዎች እንዲያዘጋጅ
- ዜጎችን ወደ ሀገር የመመለሱን እና መልሶ የማቋቋሙን ሂደት ለማቀላጠፍ መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማትና ሌሎች የዘርፉ ተዋናዮች ጋር በጋራ እንዲሰራ

**የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች፡-**

- በውጪ ሀገሮች ችግር ላይ የወደቁ ሰራተኞችን እንዲደግፉ እና ወደ ሀገራቸው የሚመለሱበትን ሁኔታ እንዲያስተባብሩ

**አለም አቀፍ እና ሀገር በቀል ሲቪል ማህበራት፡-**

- ዜጎችን ወደ ሀገር በመመለሱ ስራ የኢትዮጵያን መንግስት (በፋይናንስ እና በቴክኒክ) እንዲያግዙ
- በጋራ ሀብት በማሰባሰብ በቤይሩት እና በሌሎችም አካባቢዎች የሚገኙና የምግብ፣ ትራንስፖርት፣ ህክምና እና መጠለያ የሚያስፈልጋቸውን ዜጎች እንዲያግዙ
- ወደ ሀገራቸው ለተመለሱት የመልሶ መቋቋሚያ ድጋፎች እንዲያደርጉ

**የግሉ ዘርፍ፡-**

- ሀገር በቀል እና ግዙፍ የውጪ ሀገር ኩባንያዎች ይህንን አንገብጋቢ ጉዳይ በገንዘብ እና በአይነት እንዲደግፉ
- የተለያየ ክህሎት ላላቸው ከስደት ተመላሾች የስራ እድል እና ለሌሎችም በተለያየ የስራ ዘርፍ የሚሰማሩብት ስልጠና እንዲያመቻቹ እንጠይቃለን።

## የሲቪል ማህበራት ዝርዝር

1. ActionAid Ethiopia
2. Addis Ababa Women's Association (AAWA)
3. ANNPCAN – Ethiopia
4. CARE Ethiopia
5. Center for Accelerated Women's Economic Empowerment (CAWEE- Ethiopia)
6. Consortium of Christian Relief and Development Association (CCRDA)
7. Christian Aid
8. Consortium of Ethiopian Human Rights Organizations – (CEHRO)
9. Civil Society Support Programme Phase Two (CSSP2)
10. CVT Ethiopia
11. Forum for African Women Educationalists (FAWE - Ethiopia)
12. Emmanuel Development Association (EDA)
13. Ethiopian Civil Society Organizations Forum (ECSF)
14. Ethiopian Women Lawyers Association (EWLA)
15. Ethiopian Women with Disability National Association (EWDNA)
16. Family Service Association (FSA)
17. Gambella Women's Association
18. GOAL
19. Good Samaritan Association (GSA)
20. LIVE-ADDIS
21. Medical Collaboration Committee (CCM)
22. Network of Ethiopian Women's Associations (NEWA)
23. Network of Networks of HIV Positive
24. New Millennium Hope Development Organization (NMHDO)
25. Organization for Girls Adults Advocacy (OGAA)
26. Orphans and Girls Assistance Association (OGAA)
27. Oxfam
28. PACT Ethiopia
29. Professional Alliance for Development (PADet)
30. PELUM Ethiopia
31. PHE Ethiopia Consortium (PHEEC)
32. Plan International ETHIOPIA
33. Redeem the Generation
34. Rift valley children and women Development organization (RCWDO)
35. Siddhartha Development Ethiopia
36. Siiqqee Women's Development Association
37. Strategic Initiative for Women in the Horn of Africa (SIHA Network)
38. TIMRAN
39. The Lutheran World Federation
40. Union of Ethiopian Women Charitable Association (UEWCA)
41. Voluntary Service Overseas (VSO)
42. Women Can Do It (WCDI)
43. Young Women's Christian Association in Ethiopia (YWCA - Ethiopia)

For more information, please contact *Abiy Wendifraw ( + 251912738573) newaethiopia@gmail.com*
*Tel.: +251 11 821 7758 (Office)*